# እንኳን ወደ እንግሊዝ ሃገር በደህና መጡ

# በእንግሊዝ ሃገር ወላጅነት

(*ወላጅነት = ማለት ልጆችን በወላጅነት ማሳደግ ማለት ነው)



ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸዉ ደህና፣ ጤናማ እና ደስተኛ የሆነ ህይወት ወደፊት እንዲኖራቸዉ ይመኛሉ። ነገር ግን የተለየ ህግ፣ የተለየ ስርአት፣ ከሰዎችም የሚጠበቀዉ ነገር የተለየ የሆነበት እና የተለየ ቋንቋ በሚነገርበት አዲስ ሃገር ላይ የተለያዩ እክሎች ያጋጥማቸዋል። ይህ ሊፍሌት በእንግሊዝ አገር ዉስጥ ልጅ ስለማሳደግ መረጃ ይሰጣል። እርሶ የልጆትን ትምህርት እና የወደፊት ራእይ ለመደገፍ ይረዳዎት ዘንድ ስለትምህርት ስርአቱ መረጃ ይሰጣል። በተጨማሪም ልጆችን ከአካላዊ እና ከስነልቦናዊ ጉዳት ለመጠበቅ የወጡትን ህጎችም ይዳስሳል ፤ ይህም ወላጆች ልጆቻቸው መቆጣጠር እና መቅጣት የሚችሉባቸዉ መንገዶች ላይ ተጽኖ ያደርጋል። ይህ መረጃ የተመረጠዉ በእንግሊዝ አገር ጥገኝነት በጠየቁ ሰዎች ሲሆን ፤ መጀመሪያ ወደ እዚህ ሲመጡ ባዉቀዉ ይጠቅመኝ ነበር ካሏቸዉ ነገሮች በመነሳት ነዉ። ይህንን መረጃ በቅድሚያ ማወቅ ሊነሱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል ይረድል ፤ ለእርሶ ኖርማል የሆነዉ እዚህ ችግር ሊፈጥር ይችላል።

## ትምህርት ቤት መሄድ









በእንግሊዝ ህግ ከ5 እስከ 16 አመት ያሉ ልጆች የሙሉ ቀን ትምህርት መግባት አለባቸው እንዲሁም 16 እስከ 18 አመት የሆኑ ልጆች የሆነ አይነት ትምህርት ላይ ወይም ስልጠና ላይ መሆን አለባቸዉ። ወላጆች ልጆቻቸዉ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ የማድረግ የህግ ግዴታ አለባቸው። ይህ ምርጫ አይደለም። ከትምህርት ቤት መቅረት ልጆችን በትምህርታቸዉ ወደኋላ እንዲቀሩ ያደርጋቸዋል። ልጆችን ካለጥሩ ምክንያትን እና ትምህርት ቤቱን ሳያሳዉቁ ከትምህርት ቤት ማስቀረት የለቦትም። አለበለዚያ ወላጆች ቅጣት ሊጣልባቸው ወይም የፍርድ ቤት ማዘዣ ሊሰጣቸዉ ይችላል። ትምህርት ቤቶች የልጆችን መገኘት በቅርበት ስለሚከታተሉ ትምህርት ቤቱን እስከ 8.30 በመደወል ልጆት መምጣት እንደማይችል ያሳዉቁ። ተጨማሪ መረጃ ይህ ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል



https://www.gov.uk/browse/childcare-parenting/schools-education

## ልጆችን ከአካላዊ እና ከስነልቦናዊ ጉዳት መጠበቅ (ጥበቃ)

እንግሊዝ ሃገር ዉስጥ በአካባቢዎት ያሉት ባለስልጣናት በልጆቾ ህይወት ላይ የሚጫወቱት ሚና ከመጡበት ሃገር ሊለይ ይችላል። ብዙ ሰዎች በልጆች ህይወት ላይ ከፍ ያለ ተሳትፎ እንዳላቸዉ እና ልጆች አደጋ ላይ ከሆኑ ጣልቃ ለመግባት ከፍ ያለ ስልጣን ያላቸዉ ናቸዉ ይላሉ። ወላጆች ልጆቻቸዉ ሰላም እና ጤና እንዲሆኑ የማድረግ ሃላፊነት ቢኖርባቸዉም የአካባቢዉ ባለስልጣናት በአካባቢዎቻቸዉ ያሉትን ልጆች ደህንነት የማስጠበቅ ህጋዊ ግዴታ አለባቸዉ። ሄልዝ ቪዚተርስ፣ አስተማሪዎች፣ ሶሻል ወርከሮች፣ ሎካል ካዉንስል እና ፖሊሶች ሁሉም አደጋ ላይ የሆኑ ልጆችን ለመለየት እና ለመደገፍ የሚጫወቱት ሚና አለ። ልጆች ላይ የሚደርስ ጥቃት ወይም ቸልተኝነትን ለምሳሌ ምክኛት የሌለዉ ጉዳት፣ የስሜት ጭንቀት፣ የንጽህና ጉድለት ወይም ረሃብ ወይም ልጆች ካለጠባቂ መተዋቸዉን ይቆጣጠራሉ። ትምህርት ቤት ወይም ሄልዝ ቪዚተር ወይም ህብረተሰቡ ስለ ልጆች ጤንነት እና ደህንነት አስቦ ለፖሊስ ወይም ሶሻል ወርከር ቢያመለክት ጉዳዩን ማጣራት አለባቸው። ቤተሰቡን በመጎብኘት ችግሩን ያጣራሉ እናም ያለዉን አደጋ/ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ እንዳለበት ይገልጻሉ። ነገር ግን ልጁ ጉዳት የሚደርስበት ከመሰላቸዉ ልጁን ከቤተሰቡ ወስደው በሎካል ካዉንስል እንክብካቤ ዉስጥ እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ።



ስለዚህ በእንግሊዝ አገር ልጆችን ከጉዳት እና ከቸልተኝነት የሚጠብቀዉ ህግ ወላጆች እንዴት በቅርበት ልጆቻቸዉን መጠበቅ እና እንዴት መቅጣት እንዳለባቸው ይቆጣጠራል።

## ልጆችን መቆጣጠር



ወላጆች ልጆቻቸዉን መቆጣጠር ባለመቻላቸዉ ምክንያት ልጆች አደጋ ላይ የመዉደቅ እድላቸዉ ከፍ ካለ ቸልተኛ እንደሆኑ ይቆጠራል። ለምሳሌ ተቆጣጣሪ የሌለው የሌለዉ ልጅ አደጋን መለየት ካልቻለ፣ እንዴት መሸሽ እንዳለበት ካላወቀ ወይም በአጣዳፊ ችግር ግዜ ምን ማድረግ እንዳለበት ካለወቀ የመጎዳት እድል አለዉ። የአገር አቀፍ መመሪዎች እንድሚሉ ጨቅላ ህፃናት እና ትንንሽ ልጆች መቼም ብቻቸዉን መተዉ የለባቸዉም፤ ለ15 ደቂቃም ቢሆን። አብዛኛዉ ከ12 አመት በታች የሆኑ ልጆች ብቻቸዉን ለመተዉ፣ ትንሽ ልጆችን ለመንከባከብ ወይም ካለ አዋቂ ክትትል ለራሳቸዉ ምግብ ማብሰል አይችሉም። ከ16 አመት በታች የሆኑ ልጆች ለሊቱን ሙሉ ብቻቸዉን መተዉ የለባቸውም። ህጉ ልጆች በስንት አመታቸው ብቻቸዉን መተዉ እንደሚችሉ አይግልፅም ምክኛቱም የልጆች አስተዋይነት ከልጅ ልጅ ስለሚለያይ። ስለዚህ ወላጆች የልጆቻቸዉን አገናዛቢነት አስበዉ አደጋ የሚፈጥሩ ነገሮችን ለምሳሌ ቢላዎች ወይም ልጆች ሊወድቁባቸዉ የሚሉባቸዉን መስኮቶች ማስወገድ እና አደጋ ሲደርስ ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ ማሳወቅ አለባቸዉ።



ትናንሽ ልጆች ከቤት ዉጪ ሲጫወቱ ለምሳሌ መናፈሻ ዉስጥ ሲጫወቱም ቁጥጥር ያስፈልጋቸዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወላጆች ልጆቻቸዉን እንዲያደርሱ እና እንዲመልሱ ይጠብቃሉ። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት አንድ ልጅ ብቻዉን መቼ መሄድ እንደሚችል የሚደነግግ የራሱ ፖሊሲ አለዉ። ሌላ ሰዉ ልጆት ከትምህርት ቤት የሚወስድ ከሆነ ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ ይኖርቦታል ምክኛቱም ትምህርት ቤቱ ለማይታወቅ ሰው ለጆችን አይሰጥም።

እነዚ ነገሮች ሃገሮት ተቀባይ ከነበሩ ነገሮች ጋር ሊቃረኑ ይችላሉ፤ ልጆች አነስ ባለ እድሜያቸዉ ሃላፊነት ሊሰጣቸዉ ይችላል። ነገር ግን እንግሊዝ ዉስጥ ስላለዉ የተለየ አሰራር እና ወላጅነት ላይም ስላለዉ ተጽኖ መረዳት ያስፈልጋል። ለተጨማሪ መረጃ https://www.nspcc.org.uk/keeping-children-safe/

## ልጆችን መቅጣት



በተለያዩ ሃገሮች እንደታየዉ እንግሊዝ አገር ዉስጥ ልጆችን ለመቅጣት ተብለዉ የሚረጉ አካላዊ ቅጣቶች ለምሳሌ ስለመማታት ያለዉ አስተሳሰብ ተቀይሯል። አሁን በደል እንደሆን እና ጎጂ እንደሆነ ነዉ የሚቆጠረዉ። በአጠቃላይ መልክቱ **ወላጆች ልጆችን ስርአት ለማስያዝ ብለዉ ማንኛዉንም አይነት አካላዊ ቅጣት መፈጸም ወይም እፈጽማለዉ ብለዉ ማስፈራራት የለባቸውም።**

ማንኛዉም አይነት ቅጣት ልየጆችን ሰውነት ማሳበጥ፣ ማበለዝ፣ ማቁሰል፣ ቆዳን ማቅላት ፤ መላጥ ወይም መቧጨር የለበትም። የአካባቢዉ ባለስልጣኖች ስለ ልጅ መመታት ሪፖርት ከደረሳቸዉ ማጣራት አለባቸዉ። ልጁ ተጨማሪ ጉዳት ይደርስበታለ ብለዉ ካመኑ ልጁን ወስደዉ ወደ እንክብካቤ ማስገባት ይችላሉ።



ይህ በተለይ የሚሆነዉ ልጁ እንደ ማማሰያ፣ ቀበቶ ወይም ጫማ ባሉ እቃዎች የተመታ እንደሆነ ነዉ።

ስለዚህ ከዚህ በፊት ልጆችን ለመቅጣት አካላዊ ቅጣት ከነበረ የሚፈጽሙት፣ ወላጆች ሁኔታዉን ለመረዳት እንዲያግዛቸዉ እና ሌላ አማራጮችን እንዲጠቀሙ የሚያግዝ ሲስተም አለ። የሎካል ካዉንስሎትን የቅድሚያ እርዳታ ቡድንን ማኘት ወይም ወደዛ ሪፈር እንዲደረጉ መጠየቅ ይችላሉ። እንዴት ትምህርት እና ሽልማትን በአካላዊ ቅጣት ፈንታ መጠቀም እንደሚችሉ ያስረዶታል።

ለወላጆች የሚሆን ወርክሾች አላቸዉ እንዲሁም ቤት መጥተዉ መንገዶቹን እንዲለማመዱ ያግዞታል።

ለተጨማሪ መረጃ https://learning.nspcc.org.uk/ safeguarding-child-protection/early-help-early-intervention እና https://www.familylives.org.uk/advice/primary/behaviour/positive-discipline/




አስከፊ ነገሮች ያጋጠሟቸዉ ልጆች ለምሳሌ ጦርነትን ያዩ እና ቤታቸዉን ያጡ ልጆች ስነ ልቦናቸዉ በጣም ተነክቶ ሊሆን ስለሚችል፤ ይህንንም ማገናዘብ ያስፈልጋል። ይህም ለወላጆች የሚከብድ እና የሚያስቸግር ጸባይ ሊፈጥር ይችላል። አዋቂዎችም በፍርሃት እና በማጣት ሊጎዱ ይችላሉ እንዲሁም የጥገኝነት ጥያቄ ምላሽ ሲጠብቁም የጭንቀት እና የሰላም ማጣት ስሜት ሊፈጥር ይችላል። በዚህ ጊዜም ስረ እንዲሰሩም ስለማይፈቀድ ወላጆች ለ24 ሰአታት እና ለ 7 ቀናት ቤት ውስጥ አብረዉ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ቤት ዉስጥ ግጭት ሊፈጥር ይችላል እንዲሁም ወላጆች ከተለመደዉ በላይ በ ቁጣ ቁጣ ሊላቸዉ ይችላል። እርሶ ባለፉበት መንገድ ከዚህ በፊት ያለፉ ሰዎች እንደሚመከሩት በህይወቶ ላይ የሚሰማዎትን ጭንቀት ለመቀንስ በአካባቢዎ የማህበራዊ ግንኙነት እንዲፈጥሩ እና ከቤት ውስጥ የሚያስወጡ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፉ ይመክራሉ። ስለዚህ ጉዳይ መረጃ ከፈለጉ ሃዉዚንግ/ቤት ከሚያቀርብሎት የተሰጦትን የእንኳን ደህና መጡ ፓክ  እና የማይግሪሽን ፓርትነርሺፕ ድህረ ገጽ ያገኙታል።

ያጋጠሟቸዉ አስከፊ ሁኔታዎች ልጆቻቸዉ ላይ ስላሳደረባቸዉ ተጽኖ የተጨነቁ ወላጆች ያንግ ማይንድስ ነጻ የሆነ የእርዳታ አገልግሎትን በማግኘት ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ የባለሙያ ምክር ማግኘት ይችላሉ https://youngminds.org.uk/find-help/for-parents/parents-helpline/ ይጎብኙ።

## ከትምህርት ቤቱ እና ከሶሻል ወርከር ጋር ግንኙነት መፈጠር

ትምህርት ቤት ልጆች የጉዳት ወይም የቸልተኝነት ምልክት መኖሩን ይቆጣጠራል። አስተማሪዎች ስጋታቸዉን ማእከላዉ የኮምፒተር ሲስተም ላይ ማስቀመጥ አለባቸዉ። ትምህርች ቤቱ ወላጆችን አግኝቶ በተደጋጋሚ ወይም በተከታታይነት ስለተፈጠሩ ጉዳዮች ተወያይተዉ ምን እንደተፈጠረ ለማጣራት ይሞክራሉ። ወላጆች እየተቸገሩ ከሆነ ወይም እንግሊዝ ሃገር ምን እንደሚጠበቅ የማያዉቁ ከሆነ ትምህርት ቤቱ ከቅድሚያ እርዳታ ቡድን እገዛ ሊያደርግ ይችላል ፤ እነሱም ለቤተሰቡም የእገዛ እቅድ ያወጣሉ።ነገር ግን ወላጆች ከትምህርት ቤቱ ጋር የማይገናኙ ከሆነ እና የሚሰጠዉን ድጋፍ የማይቀበሉ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ ስጋቱን ለሶሻል ወርከር ሪፈር ያደርጋል።

አንዳንድ ነገሮች ከትምህርት ቤቱ ወደ ሶሻል ወርከሩ ወዲያዉኑ ሪፈር ይደረጋሉ። እነዚህ ጉዳዮች ከልጆች ጥቃት ጋር የተተያያዙ ሁኔታዎች ናቸዉ። ለምሳሌ አንድ ልጅ 'እናቴ መታቺኝ' ወይም 'በማማሰያ እንድምትመታኝ ነገረቺኝ' ወይም አጥጋቢ ምክንያት የሌለዉ ቁስል ወይም ምልክት ከታየ ትምህርት ቤቱ ለሶሻል ወርከር የማመልከት ግዴታ አለበት። ለዚህም ነዉ ወላጆች ወደ ትምህርት ቤቱ እስከ 8:30 ደዉለዉ ቁስሉ ወይም ምልክቱ ለምን እንደተከሰተ ማሳወቅ ያለባቸዉ። የእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚያጥራቸዉ ወላጆች ሌላ ሰዉ እንዲረዳቸዉ መጠየቅ አለባቸዉ።



ሶሻል ወርከሩ ወላጆቹን በማግኘት ችግሩን ያጣራል እናም አስፈላጊ ከሆነ የልጁን እንክብካቤ ለማሻሻል አክሽን ፕላን/መደረግ ስላለባቸዉ ነገሮች እቅድ ያወጣል። ይህ ሊያስደነግጥ ይችላል ፤ ነገር ግን መወሰድ ያለበት እርምጃ የሶሻል ወርከሩን ስጋት ማዳመጥ፣ የልጁን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ሁኔታዎችን ለመለየት በግልጽ መወያየት እና እነዚህ ጉዳዮች ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለመተግበር ፈቃደኛ መሆንን ያካትታል። ወላጆች ቤት ውስጥ የሚያደርጉትን ነገሮች መቀየር ሊያስፈልጋቸዉ ይችላል። ነገር ግን ወላጆች ዝምታን ከመረጡ ሶሻል ወርከሩ የልጁን ጤንነት ለማረጋገጥ መተግበር ያለበትን ስራ መስራት አይችልም። ነገሩ ካልተጣራ የልጁን ደህነት አደጋ ዉስጥ የሚከተውን ችግር ለመቅረፍ አይችሉም ስለዚህም ልጁ ከቤተሰቡ እንዲወሰድ ሊወስኑ ይችላሉ። ይህ እንዲፈጠር ማንም አይፈልግል። ምንም አይነት ችግር ቢሆን ወላጆች ለመወያየት እና የሚሰጣቸዉን ድጋፊ ለመቀበል ወይም የሚያድርጉትን ነገሮች ለመቀየር ፈቃደኛ ካልሆኑ ምላሹ ሁሌም ጠንከር እያለ ይሆዳል።

## በወላጆች መካከል ያለው የቤት ውስጥ ግንኙነት



ልጆች በወላጆች መካከል ግጭት ሲፈጠር ወይም ሌሎች በደሎች ሲፈፀሙ የሚያዩ ከሆነ ምንም እንኳን እነዚህ በደሎች እነሱ ላይ ባይፈጸሙም በዚህ ምክንያት አሳሳቢ እና ከፍተኛ የሆን የስነ ልቦና ቀዉስ ሊደርስባቸዉ ይችላል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት የቤት ውስጥ ግጭት ህይወታቸዉ ላይ ከፈተኛ ተጽኖ ያሳድራል በተለይም ከትንሽነትታቸው ጀምሮ ለዚህ ሁኔታ የተጋለጡ ከሆነ። ትምህርት ቤት ውስጥ ማስተዋል እንዳችሉ እና በትምህርታቸዉ እንዳይገፉ ሊያደርጋቸዉ ይችላል። እንዲሁም ድብርት እና የአመጋገብ መዛባት ሊፈጥርባቸዉ እና አስቸጋሪ ፀባይ እንዲያሳዩ ወይም ራሳቸዉ እንዲያገሉ ሊያደርጋቸዉ ይችላል። ልጆቻም ሲያድጉ ለግጭት ሊያልጣቸዉ ይችላል ወይ የድርጊቱ ፈፃሚ ወይም ተጠቂ ሊሆኑ ይችላሉ። የቤት ዉስጥ ግጭት በህግ የተከለከለ ነዉ። ፖሊስ ወይም ሶሻል ወርከሮች የቤት ውስጥ ግጭትን ሲመረምሩ ልጅ ቤት ወስጥ ካገኙ ልጁን ከተጨማሪ ጉዳት ለመጠበቅ አንደኛዉን ወላጅ ከቤት ውስጥ እንዲወጣ ለማድረግ ሊወስኑ ይችላሉ ወይም ልጁን ወስደዉ በሎካል ካዉንል እንክብካቤ ውስጥ እንዲሆን ሊወስኑ ይችላሉ።

## የሴት ልጅ ግርዛት

የሴት ልጅ ግርዛት ወይም በእንግሊዝ ሃገር እንደሚጠራዉ የሴት ልጅ ብልት ትልተላ እንዲካሄድ ማቀድ፣ መግረዝ፣ እንዲካሄድ መርዳት ወይም ማበረታት በህግ የተከለከለ ነዉ። ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የአካል እና የስነ ልቦና ጉዳት ስለሚያስከትል እንደ ልጅ ጥቃት ነዉ የሚታየዉ። ቅጣቱም አስከ 14 አመት እስር ቤት ያሳስራል።

## ልጆች እና መኪኖች



ጤናቸዉን ለመጠበቅ ሲባል ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጆች ያሉበት መኪና ውስጥ ማጨስ በህግ የተከለከለ ነዉ። ህፃናት እና ከ12 አመት በታች ወይም ከ125 ሳ.ሜ. በታች የሆኑ ልጆች በተገቢዉ የህፃናት መቀመጫ ላይ መቀመጥ አለባቸዉ። ለአስቸኳይ ጊዜ፣ ባልተጠበቀ ሰአት አጭር መንገድ ለመሄድ ወይም ታክሲ ነጂው የልጅ መቀመጫ ከሌዉ ብቻ ነዉ ይህ ሳይኖር መሄድ የሚፈቀደዉ። .



## ልጆች ህግ እንዲያከብሩ መርዳት



ወላጆች ልጆች የእንግሊዝ ሃገር ህግ ከለመዱት ህግ እንዴት እንደሚለይ እዲያዉቁ ማድረግ ይችላሉ። በህጉ መሰረት ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጆች ሲጋራ እና መጠጥ መግዛት እንደማይችሉ ያስዉቋቸዉ። የትኛዉም አዋቂ ሰዉ ይህንን ለነሱ ከገዛ ህገ ወጥ ነዉ። ማንኛዉም ሰዉ ህገ ወጥ የሆኑ እፆችን ሲጠቀም፣ ሲይዝ ወይም ሲሸጥ ከተገኘ ወይም ሌላ ሰዉ እፁን  እንዲያጓጉዙ ከሰጣቸዉ ሊያሰሩ ይችላሉ።  ከ16 አመት በታች ከሆኑ ወንድ ወይም ሴት ልጆች ጋር ፈቃደኛ ቢሆኑም የፆታ ግንኙነት ማድረግ በህግ የተከለከለ ነዉ። ከ16 አመት በላይ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር የሚደረግ ፆታዊ ግንኙነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት አለበለዚያ ግን ፆታዊ ጥቃት ወይም አስግድዶ መድፈር ይሆናል ይህም እስከ 15 አመት እስር ያስቀጣል። ወጣት ልጆች የቤተሰቦቻቸዉን ፈቃድ ካገኙ ከ16 አመታቸዉ ጀምሮ ማግባት ይችላሉ አለበለዚያ 18 አመት መሆን አለባቸዉ።

## ልጆችን ከጉልበተኞች/ቡሊ፣ ከጥላቻ እና ኢንተርኔት ላይ ከሚደርስ ጥቃት መጠበቅ

ልጆች ሌላ የትምህር ቤት ልጆች እንዴት እንደሚያረጓቸዉ እንዲነግሮት ያበረታቱ። ሌላ ልጅ የሚጠምዳቸዉ፣ የአካል እና የስነ ልቦና ጉዳት የሚያደርስባቸዉ ከሆን 'ጉልበተኝነት'/ቡሊይንግ ይባላል። በዘር ወይም በሃይማኖት ጥቃት የሚደርስባቸዉ ከሆን 'ጥላቻ'/ሄት ያባላል። እነዚህ ሁለቱም ነገሮች ለልጆች ደህንነት ላይ ጉዳት ስለሚያስከትሉ መቆም አለባቸዉ። ጉዳዩን ለማስቆም በራሶት ልጁን ወይም ወላጆቹን ለማግኘት አይሞክሩ።





የክፍል አስተማሪዉን በማናገር ስለጉዳዩ ያሳዉቁ ወደፊትም ጉዳዩ እንዳይከሰት ትምህርት ቤቱ መዉሰድ ስላለበት እርምጃ ይወያዩ።

ሁሉም ትምህርት ቤቶች የፀባይ ፖሊሲ እና ልጆትን የመከባከብ ሃላፊነት አለባቸዉ። ጥቃቱ ተመሶ ከተፈጸመ የትምህርት ቤቱን ሃላፊ / ሄድ አፍ ይር ለማናገር ይጠይቁ። ፖሊስንም ማናገር ይችላሉ በተለይ እንደ ድብደባ፣ ስርቆት፣ ማስፈራራት፣ ትንኮሳ እና እንደ ጥላቻ ላሉ ወንጀሎች።  ወላጆች ልጆቻቸዉን እንዴት ከጉልበተኞች ለመጠበቅ እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ  የሚከተለዉን ድህረ ገጽ ይጠቀሙ https://www.bullying.co.uk/bullying-at-school/advice-on-contacting-your -child-s-school-about-bullying/

ልጆች ገና ከትንሽነታቸዉ ኢንተርኔት እና ሶሻል ሚዲያ በስልካቸዉ እና በሌላ ዲጂታል ቁሳቁሶች አማካኝነት ይጠቀማሉ። በዚህም ምክንያት ተገቢ ያልሆኑ እና ጎጂ የሆኑ መረጃዎችን በማየት ለኢንተርኔት ጉልበተኝነት/ሳይበር ቡሊይንግ ወይም ጥቃት ሰለባ የመሆን እድል ይኖራቸዋል።  ይህ ለሁሉም ወላጆች ስጋት ነው፣ የልጆች ራስ መተማመን፣ ማንነት እና ጤንነት ላይም ከባድ ተጽኖ አለዉ። በድጋሚ ልጆች ያላቸዉን ስጋት እንዲያካፍሎት ያበረታቱ። ለወላጆች እነዚህን አደጋዎች ለመቆጣጠር እና ሪፖርት አድርጎ ድርጊቱ ድጋሚ እንዳይፈጸም እርምጃ እንዲወሰድ እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ምክር የሚሰጡ ድርጅቶች አሉ. ይህንን ይመልከቱ https://www.bullying.co.uk/cyberbullying/



## የወላጅ እና የልጆች መብት

የአካባቢዉ ባለስልጣን ስለልጅ ደህንነት ምርመራ እያካሄደ ከሆነ ወላጆችም ልጅም መብቶች አሏቸዉ። ባለሙያዎች ወላጆችንም ልጆችንም ያናግራሉ። ልጆች ምን እንዲደረግ እንደሚፈልጉ ያጣራሉ፣ ምክንይቱም ልጆች የወደፊት ህይወታቸዉን የሚነካ ዉሳኔ ሲተላላፈ ድምጻቸዉ መሰማት ስላለበት። ወላጆች የሚሰጣቸዉን መረጃ እንዲረዱት እና ራሳቸውን በትክክል እንዲገልጹ አስተርጓሚ እንዲኖር መጠየቅ ይችላሉ።






መፈረም ያለቦት ትርጉሙ እና ውጤቱ ምን እንደሆነ የተረዱትን ሰነድ ብቻ ነዉ። የጥበቃ መዝገብ ከተከፈተ ወላጆች በቤተሰብ ህግ ጠበቃ የህግ ተወካይነት ማግኘት ይችላሉ። እርሶ በበሆም አፊስ አሳይለም ሰፖርት ስር ከሆኑ አገልግሎቱ በህግ አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ መሰረት ነፃ ሊሆን ይችላል።  ሶሻል ወርከሩ ስለዚህ መረጃ ሊሰጦት ይገባል እንዲሁም ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ መረጃም በአቅራቢያዎ ከሚገኘዉ የዜጎች ምክር ቢሮ ማግኘት ይችላሉ።




በዚህ ሊፍሌት ላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ዙሪያ ሙሉ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ መረጃዉን በኖርዝ ኢስት ፓርትነርሺፕ ድህረ ግጽ ላይ 'ወላጅነት በእንግሊዝ'/ፓረንቲንግ ኢን ዘ ዩኬ' በሚለዉን የኢንተርኔት መማሪያን በመጠቀም ያገኙታል። https://www.nemp.org.uk/